# ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ
# እና
# ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን የእነኝህን የሁለት ቅዱሳን ሰማዕታት አባቶች መታሰቢያ በየዓመቱ ሐምሌ ፭ ቀን በታላቅ አክብሮት ታከብረዋለች። ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ እና ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ እጅግ ሊያስተውሉት የሚገባ ልዩነት እና ተመሳሳይነት አላቸው።

## የሚለያዩበት መሠረታዊ ነጥቦች፦

### ፩- ለአገልግሎት የተጠሩበት ሁኔታ፦

**ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ** ኢየሱስ ክርስቶስ አብረውት እንዲሠሩ ለአገልግሎት ከመረጣቸው ሐዋርያት መካከል የመጀመርያው ነው። የአሥራ ሁለቱም ሐዋርያት ስም ይህ ነው ፤ መጀመሪያው ጴጥሮስ የተባለው ስምዖን ወንድሙ እንድርያስም ፥ የዘብዴዎስ ልጅ ያዕቆብም ወንድሙ ዮሐንስም ፥ ፊልጶስም በርተሎሜዎስም ፥ ቶማስም ቀራጩ ማቴዎስም ፥ የእልፍዮስ ልጅ ያዕቆብም ታዴዎስም የተባለው ልብድዮስ ፥ ቀነናዊውም ስምዖን ደግሞም አሳልፎ የሰጠው የአስቆሮቱ ይሁዳ። (ማቴ.፲፥፪)

**ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ** ጌታ ለአገልግሎት ከመረጣቸው ከአሥራ ሁለቱ መካከል ብቻ ሳይሆን ከሰባው አርድእትም እንደ አንዱ አልነበረም። ጌታ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስን የመረጠው ከጌታ ትንሣኤ በኋላ ነው። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ለአገልግሎት ከመመረጡ በፊት የጌታ ተከታይ አልነበረም ፤ በዚህም የተነሳ እንዲህ ሲል መልእክቱን አስተላልፏል፦ *ለኬፋም ታየ በኋላም ለአሥራ ሁለቱ ፤ ከዚያም በኋላ ከአምስት መቶ ለሚበዙ ወንድሞች በአንድ ጊዜ ታየ ፤ ከእነርሱም የሚበዙቱ እስከ አሁን አሉ አንዳንዶች ግን አንቀላፍተዋል ፤ ከዚያም በኋላ ለያዕቆብ ኋላም ለሐዋርያት ሁሉ ታየ ፤ ከሁሉም በኋላ እንደ ጭንጋፍ ለምሆን ለእኔ ደግሞ ታየኝ። እኔ ከሐዋርያት ሁሉ የማንስ ነኝና ፥ የእግዚአብሔርን ቤተ ክርስቲያን ስላሳደድሁ ሐዋርያ ተብዬ ልጠራ የማይገባኝ ፤ ነገር ግን በእግዚአብሔር ጸጋ የሆንሁ እኔ ነኝ ፤ ለእኔም የተሰጠኝ ጸጋው ከንቱ አልነበረም ከሁላቸው ይልቅ ግን ደከምሁ ፥ ዳሩ ግን ከእኔ ጋር ያለው የእግዚአብሔር ጸጋ ነው እንጂ እኔ አይደለሁም።* (፩ቆሮ.፲፭፥፰-፲) እንግዲህ በአገልግሎት ብቁ ለመሆን ቀድሞ እና በኋላ መጠራት ልዩነት የለውም። መጥምቁ ዮሐንስ በአመጣጡ ከብሉይ ኪዳን ነብያት ሁሉ የመጨረሻው ቢሆንም ጌታ ግን ሲመሰክርለት፦ *እውነት እላችኋለሁ ፥ ከሴቶች ከተወለዱት መካከል ከመጥምቁ ዮሐንስ የሚበልጥ አልተነሣም ፤ በመንግሥተ ሰማያት ግን ከሁሉ የሚያንሰው ይበልጠዋል።* (ማቴ.፲፩፥፲፩) ብሏል።

### ፪- የትውልድ ቦታቸው፦

**ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ** የተወለደው በቤተሳይዳ ሲሆን ወላጆቹ በቅፍርናሆም ነዋሪ ነበሩ። *ፊልጶስም ከእንድርያስና ከጴጥሮስ ከተማ ከቤተ ሳይዳ ነበረ።* (ዮሐ.፩፥፵፭)

**ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ** የተወለደው ጠርሴስ በተባለ ከተማ ነው። ሐዋርያውም ስለ ትውልድ ሥፍራው ሲናገር፦ *እኔ የኪልቅያ በምትሆን በጠርሴስ የተወለድሁ ፥ በዚችም ከተማ በገማልያል እግር አጠገብ ያደግሁ ፥ የአባቶችንም ሕግ ጠንቅቄ የተማርሁ ፥ ዛሬውንም እናንተ ሁሉ እንድትሆኑ ለእግዚአብሔር ቀናተኛ የሆንሁ አይሁዳዊ ሰው ነኝ።* (ሐዋ.፳፪፥፫) ብሏል።

Copyright © 2009 Debre Selam Medhanealem Ethiopian Orthodox Tewahedo Church 4401 Minnehaha Avenue South Minneapolis, Minnesota 55406 Tel. (612) 721-1222 (U.S.A)

## ፫- የጋብቻ ሁኔታ፦

**ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ** ሚስት ያገባ ሰው ነው። በመጽሐፍ ቅዱስም እንዲህ ሲል ተጽፏል፦ *ኢየሱስም ወደ ጴጥሮስ ቤት ገብቶ አማቱን በንዳድ ታማ ተኝታ አያት ፤ እጅዋንም ዳሰሰ ፥ ንዳዱም ለቀቃት ፤ ተነሥታም አገለገለቻቸው።* *(ማቴ.፰:፲፬-፲፭)* *እንደ ሌሎቹ ሐዋርያትና እንደ ጌታ ወንድሞች እንደ ኬፋም ፥ እኅት ሚስታችንን ይዘን ልንዞር መብት የለንምን?* ፩ቆሮ.፱:፭

**ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ** ሚስት ያላገባ ድንግላዊ ነው። በመጽሐፍ ቅዱስም እንዲህ ሲል ተጽፏል፦ *ሰው ሁሉ እንደ እኔ ሊሆን እወዳለሁና ፤ ነገር ግን እያንዳንዱ ከእግዚአብሔር ለራሱ የጸጋ ስጦታ አለው ፥ አንዱ እንደዚህ ሁለተኛውም እንደዚያ። ላላገቡና ለመበለቶች ግን እላለሁ። እንደ እኔ ቢኖሩ ለእነርሱ መልካም ነው ፤* (፩ቆሮ.፯:፯-፰)

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስም ስለ አገልግሎት ባስተማረበት ትምህርቱና በደነገገው ሕግ፦ *ብቻ ለእያንዳንዱ እግዚአብሔር እንደ ከፈለለት እያንዳንዱም እግዚአብሔር እንደ ጠራው እንዲሁ ይመላለስ። እንዲሁም በአብያተ ክርስቲያናት ሁሉ እደነግጋለሁ። እያንዳንዱ በተጠራበት መጠራት እንደዚሁ ይኑር።* (፩ቆሮ.፯:፲፯ እና ፳) ብሏል። ይህም አባባል የሚያስረዳን ማግባትም ሆነ አለማግባት ለአገልግሎት እንቅፋት አለመሆኑን ነው። እያንዳንዱ በየተጠራበት አጠራር ማገልገል እንደሚገባው ግን ያሳስበናል።

**ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ** አገልግሎቱን የጀመረው በፍቅር እና በእውነት ነው።

**ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ** ቤተክርስቲያን እና የክርስቶስ ተከታዮችን በማሳደድ እና በጠላትነት ላይ ሳለ ነበር አገልግሎቱን የጀመረው ፤ ለዚህም፦ *በምድርም ላይ ወድቆ ሳለ። ሳውል ሳውል ፥ ስለ ምን ታሳድደኛለህ? የሚለውን ድምፅ ሰማ። ጌታ ሆይ ፥ ማን ነህ? አለው። እርሱም። አንተ የምታሳድደኝ እኔ ኢየሱስ ነኝ ፤ የመውጊያውን ብረት ብትቃወም ለአንተ ይብስብሃል* አለው። (ሐዋ.፱:፬-፭)

**ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ** አሣ አጥማጅ ነው። በገሊላ ባሕር አጠገብ ሲመላለስም ሁለት ወንድማማች ጴጥሮስ የሚሉትን ስምዖንን ወንድሙንም እንድርያስን መረባቸውን ወደ ባሕር ሲጥሉ አየ ፥ ዓሣ አጥማጆች ነበሩና። (ማቴ.፬:፲፰) በመሆኑም ቅዱስ ጴጥሮስ በትምህርት ያልገፋ እና ያልተማረ ሰው ነው። ነገር ግን እግዚአብሔር ጥበበኞችን እንዲያሳፍር የዓለምን ሞኝ ነገር መረጠ ፤ ብርቱንም ነገር እንዲያሳፍር እግዚአብሔር የዓለምን ደካማ ነገር መረጠ ፤ (፩ቆሮ.፩:፳፯) ተብሎ ከተነገረላቸው ሰዎችም እንደ አንዱ ነው። በሌላ መልኩም የካህናት አለቆችና ሹማምንቶች ጴጥሮስና ዮሐንስም በግልጥ እንደ ተናገሩ ባዩ ጊዜ ፥ መጽሐፍን የማያውቁና ያልተማሩ ሰዎች እንደ ሆኑ አስተውለው አደነቁ ፥ ከኢየሱስም ጋር እንደ ነበሩ አወቁአቸው። (ሐዋ.፬:፲፫)

**ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ** ግን ፈጽሞ የተማረና ሕግንም ጠንቅቆ ያውቅ የነበረ ሰው ነው። እርሱም ስለ እራሱ እንዲህ ሲል መስክሯል፦ *እኔ የኪልቅያ በምትሆን በጠርሴስ የተወለድሁ ፥ በዚችም ከተማ በገማልያል እግር አጠገብ ያደግሁ ፥ የአባቶችንም ሕግ ጠንቅቄ የተማርሁ ፥ ዛሬውንም እናንተ ሁሉ እንደትሆኑ ለእግዚአብሔር ቀናተኛ የሆንሁ አይሁዳዊ ሰው ነኝ።* (ሐዋ.፳፪:፫)

በሌላ መልኩም ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ፍጹም የተማረ ለመሆኑ ፊስጦስ የተባለ ሰው ሲመሰክርለት እናያለን፦ እንዲህም ብሎ ስለ ራሱ ሲመልስ ፊስጦስ በታላቅ ድምፅ፦ *ጳውሎስ ሆይ ፥ አብድሃል እኮ ፤ ብዙ ትምህርትህ ወደ እብደት ያዞርሃል* አለው። (ሐዋ.፳፮:፳፬) እዚህ ላይ ልናስተውለው የሚገባ አብይ ጉዳይ ቢኖር ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ለመግባት

Copyright © 2009 Debre Selam Medhanealem Ethiopian Orthodox Tewahedo Church 4401 Minnehaha Avenue South Minneapolis, Minnesota 55406 Tel. (612) 721-1222 (U.S.A)

መመዘኛው ተራ ሰው ወይም የተማረ ሰው መሆን ሳይሆን ፤ ለእግዚአብሔር መገልገያ መሣሪያ ሆኖ መገኘት ብቻ ነው። ሁለቱ ሐዋርያት ከአጠራራቸው ጀምሮ የተለያየ ሁኔታ ቢታይባቸውም ለእግዚአብሔር አገልግሎት ግን በተሰጣቸው የሥራ ድርሻ በታማኝነት ያገለገሉ ናቸው። ሁለቱም የእግዚአብሔር አገልጋዮች የእግዚአብሔርን መንግሥት የሰበኩት በተለያየ ሥፍራ ለተለያዩ ሰዎች ነው። ይህንንም ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ሲገልጸው፦ *ተመልሰው ግን ጴጥሮስ ለተገረዙት የሆነው ወንጌል አደራ እንደ ተሰጠው እንዲሁ ለእኔ ላልተገረዙት የሆነው ወንጌል አደራ እንደ ተሰጠኝ አዩ ፤ ለተገረዙት ሐዋርያ እንዲሆን ለጴጥሮስ የሠራለት ፥ ለእኔ ደግሞ ለአሕዛብ ሐዋርያ እንድሆን ሠርቶአልና።* (ገላ.፪፡፯-፰) ብሏል። ጳውሎስም ጌታ ያለውን ሲያስረዳ፦ *እርሱም። ሂድ ፥ እኔ ወደ አሕዛብ ከዚህ ወደ ሩቅ እልክሃለሁና አለኝ።* (ሐዋ.፳፪፡፳፩) እንዳለና በሌላም ሥፍራ ላይ ጌታ ለአገልግሎት እንዴት እንዳሰማራው አስረድቷል፦ በሁለተኛውም ሌሊት ጌታ በአጠገቡ ቆሞ። *ጳውሎስ ሆይ ፥ በኢየሩሳሌም ስለ እኔ እንደ መሰከርህ እንዲሁ በሮሜም ትመሰክርልኝ ዘንድ ይገባሃልና አይዞህ አለው።* (ሐዋ.፳፫፡፲፩) ይላል።

## ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ ስምንት ምዕራፎችን የያዘ ሁለት መልእክታትን ጽፏል።

## ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ አንድ መቶ ምዕራፎችን የያዘ ፲፬ መልእክታትን ጽፏል።

**ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ** በችኩልነቱ ይታወቃል። ለችኩልነቱም መነሻው ጌታን የመከተል ጽኑ ፍላጎት ስላለውና እጅግ ለአገልግሎቱም ቀናኢ ስለሆነ ነው። ጌታ ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስን አንተ የእግዚአብሔር ልጅ ነህ ብሎ ስለመሰከረለት እንዲህ ሲል አመስግኖታል፦ *እርሱም። እናንተስ እኔን ማን እንደ ሆንሁ ትላላችሁ? አላቸው። ስምዖን ጴጥሮስም መልሶ። አንተ ክርስቶስ የሕያው እግዚአብሔር ልጅ ነህ አለ። ኢየሱስም መልሶ እንዲህ አለው። የዮና ልጅ ስምዖን ሆይ ፥ በሰማያት ያለው አባቴ እንጂ ሥጋና ደም ይህን አልገለጠልህምና ብፁዕ ነህ። እኔም እልሃለሁ ፥ አንተ ጴጥሮስ ነህ ፥ በዚችም ዓለት ላይ ቤተ ክርስቲያኔን እሠራለሁ ፥ የገሃነም ደጆችም አይችሉአትም። የመንግሥተ ሰማያትንም መክፈቻዎች እሰጥሃለሁ ፤ በምድር የምታስረው ሁሉ በሰማያት የታሰረ ይሆናል ፥ በምድርም የምትፈታው ሁሉ በሰማያት የተፈታ ይሆናል።* (ማቴ.፲፮፡፲፭-፲፱) በአንጻሩም ጌታ ብዙ ጊዜ ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስን ገስጾታል።

- ከዚያን ቀን ጀምሮ ኢየሱስ ወደ ኢየሩሳሌም ይሄድ ዘንድ ከሽማግሎችና ከካህናት አለቆች ከጻፎችም ብዙ መከራ ይቀበልና ይገደል ዘንድ በሦስተኛውም ቀን ይነሣ ዘንድ እንዲገባው ለደቀ መዛሙርቱ ይገልጥላቸው ጀመር። ጴጥሮስም ወደ እርሱ ወስዶ። አይሁንብህ ጌታ ሆይ ፤ ይህ ከቶ አይደርስብህም ብሎ ሊገሥጸው ጀመረ። *እርሱ ግን ዘወር ብሎ ጴጥሮስን። ወደ ኋላዬ ሂድ ፥ አንተ ሰይጣን ፤ የሰውን እንጂ የእግዚአብሔርን አታስብምና ዕንቅፋት ሆነህብኛል* አለው። ማቴ. ፲፮፡፳፩-፳፫

- ጴጥሮስም። የእኔን እግር ለዘላለም አታጥብም አለው። ኢየሱስም። *ካላጠብሁህ ፥ ከእኔ ጋር ዕድል የለህም ብሎ መለሰለት።* ስምዖን ጴጥሮስም። ጌታ ሆይ ፥ እጆችንና ራሴን ደግሞ እንጂ እግሬን ብቻ አይደለም አለው። ኢየሱስም። የታጠበ እግሩን ከመታጠብ በቀር ሌላ አያስፈልገውም ፥ ሁለንተናው ግን ንጹሕ ነው ፤ እናንተም ንጹሐን ናችሁ ፥ ነገር ግን ሁላችሁ አይደላችሁም አለው። (ዮሐ.፲፫፡፰-፲)

- *ስምዖን ጴጥሮስም* ሰይፍ ስለ ነበረው መዘዘው ፥ የሊቀ ካህናቱንም ባርያ መትቶ ቀኝ ጆሮውን ቈረጠ ፤ የባርያውም ስም ማልኮስ ነበረ። ኢየሱስም ጴጥሮስን። ሰይፍህን ወደ ሰገባው ክተተው ፤ አብ የሰጠኝን ጽዋ አልጠጣትምን? አለው። (ዮሐ.፲፰፡፲፡፲፩ ) ተብሎ የተጻፈ ሲሆን በሌላ ቦታም ጌታ ቅዱስ ጴጥሮስን ሲናገረው እና ስለሠራው ነገር ሲገስጸው እንዲህ ብሎታል፦ እነሆም ፥ ከኢየሱስ ጋር ከነበሩት አንዱ እጁን ዘርግቶ ሰይፉን መዘዘና የሊቀ ካህናቱን ባሪያ መትቶ ጆሮውን ቈረጠው። በዚያን ጊዜ ኢየሱስ እንዲህ አለው። ሰይፍ የሚያነሡ ሁሉ በሰይፍ ይጠፋሉና ሰይፍህን ወደ ስፍራው መልስ። (ማቴ.፳፮፡፶፩-፶፪)

- ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ ምንም እንኳን ችኩል ቢሆንም ከጌታ ትንሣኤ በኋላ እና ከመንፈስ ቅዱስ መውረድ በኋላ ብዙ ድንቅ ነገርን አድርጓል። ኢየሱስ ክርስቶስ ስላደረገውም በገሐድ ሲመሰክር እንዲህ ብሏል፦ የእስራኤል ሰዎች ሆይ ፥ ይህን ቃል ስሙ ፤ ራሳችሁ እንደምታውቁ ፥ የናዝሬቱ ኢየሱስ እግዚአብሔር በመካከላችሁ በእርሱ በኩል ባደረገው ተአምራትና በድንቆች በምልክቶችም ከእግዚአብሔር ዘንድ ለእናንተ የተገለጠ ሰው ነበረ ፤ እርሱንም በእግዚአብሔር በተወሰነው አሳቡና በቀደመው እውቀቱ ተሰጥቶ በዓመፀኞች እጅ ሰቅላችሁ ገደላችሁት። (ሐዋ.፪፡፳፪-፳፫)በማለት ምስክርነቱን ሰጥቷል።

- በሌላ በኩልም ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ በሰጠው ትምህርት፦ ጴጥሮስም አይቶ ለሕዝቡ እንዲህ ሲል መለሰ፦ የእስራኤል ሰዎች ሆይ ፥ በዚህ ስለ ምን ትደነቃላችሁ? ወይስ በገዛ ኃይላችን ወይስ እግዚአብሔርን በመፍራታችን ይህ ይመላለስ ዘንድ እንዳደረግነው ስለ ምን ትኩር ብላችሁ ታዩናላችሁ? የአብርሃምና የይስሐቅ የያዕቆብም አምላክ ፥ የአባቶቻችን አምላክ ፥ እናንተ አሳልፋችሁ የሰጣችሁትንና ሊፈታው ቈርጦ ሳለ በጲላጦስ ፊት የካዳችሁትን ብላቴናውን ኢየሱስን አከበረው። እናንተ ግን ቅዱሱን ጻድቁንም ክዳችሁ ነፍሰ ገዳዩን ሰው ይሰጣችሁ ዘንድ ለመናችሁ ፥ የሕይወትንም ራስ ገደላችሁት ፤ እርሱን ግን እግዚአብሔር ከሙታን አስነሣው ፥ ለዚህም ነገር እኛ ምስክሮች ነን። በስሙም በማመን ይህን የምታዩትንና የምታውቁትን የእርሱ ስም አጸናው ፥ በእርሱም በኩል የሆነው እምነት በሁላችሁ ፊት ይህን ፍጹም ጤና ሰጠው። (ሐዋ.፫፡፲፪-፲፮)ከማለት ባሻገር ያለማመንታትና ያለመወላወል ጌታን ማገልገል እንዴት እንደሚገባ ሲናገርም፦ ጴጥሮስና ሐዋርያትም መልሰው አሉ። ከሰው ይልቅ ለእግዚአብሔር ልንታዘዝ ይገባል።(ሐዋ.፭፡፳፱)በማለት መልስ መስጠቱን እንረዳለን።

  ምንም እንኳን ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስን የእምነት አዕማድ እያለ ቢመሰክርለትም በአሠራራቸው እና በአካሄዳቸው ልዩነት የተነሣ አንድ ጊዜ ቅዱስ ጳውሎስ ቅዱስ ጴጥሮስን በይፋ እንዲህ ሲል ገስጾታል፦

  ነገር ግን ኬፋ ወደ አንጾኪያ በመጣ ጊዜ ፊት ለፊት ተቃወምሁት ፥ ይፈረድበት ዘንድ ይገባ ነበርና። አንዳንድ ከያዕቆብ ዘንድ ሳይመጡ ከአሕዛብ ጋር አብሮ ይበላ ነበርና ፤ በመጡ ጊዜ ግን ከተገረዙት ወገን ያሉትን ፈርቶ ያፈገፍግ ነበርና ከእነርሱ ተለየ። የቀሩትም አይሁድ ደግሞ ፥ በርናባስ ስንኳ በግብዝነታቸው እስከ ተሳበ ድረስ ፥ ከእርሱ ጋር አብረው ግብዞች ሆኑ። ነገር ግን እንደ ወንጌል እውነት በቅንነት እንዳልሄዱ ባየሁ ጊዜ በሁሉ ፊት ኬፋን። አንተ አይሁዳዊ ሳለህ በአይሁድ ኑሮ ያይደለ በአሕዛብ ኑሮ ብትኖር ፥ አሕዛብ በአይሁድ ኑሮ ሊኖሩ እንዴት ግድ አልሃቸው? አልሁት።
  (ገላ.፪፡፲፩-፲፬)

## የሚመሳሰሉበት መሠረታዊ ነጥቦች፦

### ፩- ሁለቱም አይሁዳውያን ናቸው፦

ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ አይሁዳዊ ለመሆኑ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ የጻፈውን መልእክት ማንበብ ግድ ይላል፦ *ነገር ግን እንደ ወንጌል እውነት በቅንነት እንዳልሄዱ ባየሁ ጊዜ በሁሉ ፊት ኬፋን። አንተ አይሁዳዊ ሳለህ በአይሁድ ኑሮ ያይደለ በአሕዛብ ኑሮ ብትኖር ፥ አሕዛብ በአይሁድ ኑሮ ሊኖሩ እንዴት ግድ አልሃቸው? አልሁት።* (ገላ.፪፡፲፬)

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ አይሁዳዊ ለመሆኑ እንዲህ በማለት ባስተላለፈው መልእክት ለማወቅ ይቻላል፦ *በስምንተኛው ቀን የተገረዝሁ ፥ ከእስራኤል ትውልድ ፥ ከብንያም ወገን ፥ ከዕብራውያን ዕብራዊ ነኝ ፤ ስለ ሕግ ብትጠይቁ ፥ ፈሪሳዊ ነበርሁ ፤* (ፊልጵ.፫፡፭)

Copyright © 2009 Debre Selam Medhanealem Ethiopian Orthodox Tewahedo Church 4401 Minnehaha Avenue South Minneapolis, Minnesota 55406 Tel. (612) 721-1222 (U.S.A)

## ፪- ሁለቱም በጌታ የተጠሩ ናቸው፦

**ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ** የተጠራው አሳ ሲያጠምድ ነው። ጌታ በገሊላ ባሕር አጠገብ ሲመላለስም ሁለት ወንድማማች ጴጥሮስ የሚሉትን ስምዖንን ወንድሙንም እንድርያስን መረባቸውን ወደ ባሕር ሲጥሉ አየ ፤ ዓሣ አጥማጆች ነበሩና። እርሱም። በኋላዬ ኑና ሰዎችን አጥማጆች እንድትሆኑ አደርጋችኋለሁ አላቸው። ወዲያውም መረባቸውን ትተው ተከተሉት። ማቴ.፬፥፲፰-፳

**ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ** በጌታ የተጠራው ወደ ደማስቆ ይጓዝ በነበረበት ጊዜ ነው። ሳውል ግን የጌታን ደቀ መዛሙርት እንዲገድላቸው ገና እየዛተ ወደ ሊቀ ካህናት ሄደ ፤ በዚህ መንገድ ያሉትንም ሰዎች ወንዶችንም ሴቶችንም ቢያገኝ ፤ እያሰረ ወደ ኢየሩሳሌም ያመጣቸው ዘንድ በደማስቆ ላሉት ምኵራቦች ደብዳቤ ከእርሱ ለመነ። ሲሄድም ወደ ደማስቆ በቀረበ ጊዜ ድንገት በእርሱ ዙሪያ ከሰማይ ብርሃን አንጸባረቀ ፤ በምድርም ላይ ወድቆ ሳለ። ሳውል ሳውል ፤ ስለ ምን ታሳድደኛለህ? የሚለውን ድምፅ ሰማ። ጌታ ሆይ ፤ ማን ነህ? አለው። እርሱም። አንተ የምታሳድደኝ እኔ ኢየሱስ ነኝ ፤ የመውጊያውን ብረት ብትቃወም ለአንተ ይብስብሃል አለው። (ሐዋ.፱፥፩-፭)

**ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ** በጌታ ከተጠራ በኋላ ጌታ ወደ አናንያ ዘንድ ሄደ። ጳውሎስ በጌታ እንደተጠራው ሁሉ በመንፈስ ቅዱስም ተጠርቷል፦ በአንጾኪያም ባለችው ቤተ ክርስቲያን ነቢያትና መምህራን ነበሩ ፤ እነርሱም በርናባስ ፤ ኔገር የተባለው ስምዖንም ፤ የቀሬናው ሉክዮስም ፤ የአራተኛው ክፍል ገዥ የሄሮድስም ባለምዋል ምናሔ ፤ ሳውልም ነበሩ። እነዚህም ጌታን ሲያመልኩና ሲጦሙ መንፈስ ቅዱስ። በርናባስንና ሳውልን ለጠራኋቸው ሥራ ለዩልኝ አለ። (ሐዋ.፲፫፥፩-፪)

የዚህን ቃል እውነተኛነት ሐዋርያው ጳውሎስ ሲያጸናው እንዲህ ነበር ያለው፦ *ነገር ግን በእናቴ ማኅፀን ሳለሁ የለየኝ በጸጋውም የጠራኝ እግዚአብሔር በአሕዛብ መካከል ስለ እርሱ ወንጌልን እሰብክ ዘንድ ልጁን በእኔ ሁኔታ ሊገልጥ በወደደ ጊዜ ፤ ወዲያው ከሥጋና ከደም ጋር አልተማከርሁም ፤ ከእኔም በፊት ሐዋርያት ወደ ነበሩት ወደ ኢየሩሳሌም አልወጣሁም ፤ ነገር ግን ወደ ዓረብ አገር ሄድሁ እንደ ገናም ወደ ደማስቆ ተመለስሁ።*(ገላ.፩-፲፭-፲፯)

በዚህ ጥቅስ ላይ የምንረዳው አብይ ነገር ቢኖር ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ በእግዚአብሔር አብ ፤ በእግዚአብሔር ወልድ እና በእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ተጠርቷል።

## ፫- ሁለቱንም ጌታ ስማቸውን ለውጦታል፦

**ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ** አስቀድሞ የዮና ልጅ ስምዖን ተብሎ ይጠራ ነበር። (ዮሐ.፳፩፥፲፭)ጌታም ጴጥሮስ ብሎ ስያሜ አወጣለት። *የዮና ልጅ ስምዖን ሆይ ፤* በሰማያት ያለው አባቴ እንጂ ሥጋና ደም ይህን አልገለጠልህምና ብፁዕ ነህ። እኔም እልሃለሁ ፤ አንተ ጴጥሮስ ነህ ፤ በዚችም ዓለት ላይ ቤተ ክርስቲያኔን እሠራለሁ ፤ የገሃነም ደጆችም አይችሉአትም። (ማቴ.፲፮፥፲፯-፲፰)

**ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ** አስቀድሞ ለአገልግሎት ሲጠራ ስሙ *ሳውል* ተብሎ ይጠራ ነበር። በምድርም ላይ ወድቆ ሳለ ሳውል ሳውል ፤ ስለ ምን ታሳድደኛለህ? የሚለውን ድምፅ ሰማ።(ሐዋ.፱፥፬)

በአገልግሎቱ ጽናት ጳውሎስ የሚል ስያሜ ተሰጠው። በሁለተኛውም ሌሊት ጌታ በአጠገቡ ቆሞ። *ጳውሎስ ሆይ ፤* በኢየሩሳሌም ስለ እኔ እንደ መሰከርህ እንዲሁ በሮሜም ትመሰክርልኝ ዘንድ ይገባሃልና አይዞህ አለው። (ሐዋ.፳፫፥፲፩)

Copyright © 2009 Debre Selam Medhanealem Ethiopian Orthodox Tewahedo Church 4401 Minnehaha Avenue South Minneapolis, Minnesota 55406 Tel. (612) 721-1222 (U.S.A)

## ፬- ሁለቱም መንፈስ ቅዱስን ተቀብለው በልሳን ተናግረዋል፦

**ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ** ጌታ ባረገ በአሥረኛው ቀን መንፈስ ቅዱስ ለሐዋርያት ሲወርድ ያን ጊዜ መንፈስ ቅዱስን ተቀብሏል ፤ በተለየ ቋንቋም ተናግሯል፦ በዓለ ኀምሳ የተባለውም ቀን በደረሰ ጊዜ ፥ ሁሉም በአንድ ልብ ሆነው አብረው ሳሉ ፥ ድንገት እንደሚነጥቅ ዓውሎ ነፋስ ከሰማይ ድምፅ መጣ ፥ ተቀምጠው የነበሩበትንም ቤት ሁሉ ሞላው። እንደ እሳትም የተከፋፈሉ ልሳኖች ታዩአቸው ፤ በያንዳንዳቸውም ላይ ተቀመጡባቸው። በሁሉም መንፈስ ቅዱስ ሞላባቸው ፥ መንፈስም ይናገሩ ዘንድ እንደ ሰጣቸው በሌላ ልሳኖች ይናገሩ ጀመር። (ሐዋ. ፪፡፩-፬)

**ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ** ስለ መንፈስ ቅዱስ ስጦታ ሲናገር፦ *ከሁላችሁ ይልቅ በልሳኖች እናገራለሁና እግዚአብሔርን አመሰግናለሁ ፤* (፩ቆሮ.፲፬፡፲፰) በሌላ ሥፍራም እንዲህ ያለ የምስክርነት ቃል ስለ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ተነግሯል፦ *ጠንቋዩ ግን ኤልማስ ፥ ስሙ እንዲሁ ይተረጐማልና ፥ አገረ ገዢን ከማመን ሊያጣምም ፈልጎ ተቃወማቸው። ጳውሎስ የተባለው ሳውል ግን መንፈስ ቅዱስን ተሞልቶ ትኵር ብሎ ሲመለከተው። አንተ ተንኰል ሁሉ ክፋትም ሁሉ የሞላብህ ፥ የዲያብሎስ ልጅ ፥ የጽድቅም ሁሉ ጠላት ፥ የቀናውን የጌታን መንገድ ከማጣመም አታርፍምን? አሁንም ፥ እነሆ ፥ የጌታ እጅ በአንተ ላይ ናት ፥ ዕውርም ትሆናለህ እስከ ጊዜውም ፀሐይን አታይም አለው። ያን ጊዜም ጭጋግና ጨለማ ወደቀበት ፥ በእጁም የሚመራውን እየዞረ ፈለገ።* (ሐዋ.፲፫፡፱-፲፩)

## ፭- ሁለቱም መንፈስ ቅዱስን ለመስጠት ኃይል ነበራቸው፦

በኢየሩሳሌም የነበሩ ሐዋርያት የሰማርያ ሰዎች የእግዚአብሔርን ቃል እንደተቀበሉ በሰሙ ጊዜ **ጴጥሮስና ዮሐንስን** ሰደዱላቸው። ጴጥሮስና ዮሐንስም፦ እነርሱም በወረዱ ጊዜ መንፈስ ቅዱስን ይቀበሉ ዘንድ ጸለዩላቸው ፤ በጌታ በኢየሱስ ስም ብቻ ተጠምቀው ነበር እንጂ ከእነርሱ በአንዱ ላይ ስንኳ ገና አልወረደም ነበርና። በዚያን ጊዜ እጃቸውን ጫኑባቸው መንፈስ ቅዱስንም ተቀበሉ። (ሐዋ.፰፡፲፮-፲፯)

**ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ** ወደ ኤፌሶን ከመጣ በኋላ በዮሐንስ ጥምቀት የተጠመቁትን አንዳንድ ደቀ መዛሙርትን ስለ መንፈስ ቅዱስ ጠይቋቸው በጌታ ኢየሱስ ስም ከተጠመቁ በኋላ፦ ጳውሎስም እጁን በጫነባቸው ጊዜ መንፈስ ቅዱስ ወረደባቸው በልሳኖችም ተናገሩ ፥ ትንቢትም ተናገሩ። ሰዎቹም ሁሉ አሥራ ሁለት ያህሉ ነበር። (ሐዋ.፲፱፡፮-፯)

## ፮- ሁለቱም ድንቅና ተአምራትን አድርገዋል፦

**ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ** ስላደረገው ድንቅ እንዲህ ተብሎ በቅዱስ መጽሐፍ ተጽፏል፦ *ጴጥሮስም በየስፍራው ሁሉ ሲዞር በልዳ ወደሚኖሩ ቅዱሳን ደግሞ ወረደ። በዚያም ከስምንት ዓመት ጀምሮ በአልጋ ላይ ተኝቶ የነበረውን ኤንያ የሚሉትን አንድ ሰው አገኘ ፤ እርሱም ሽባ ነበረ። ጴጥሮስም። ኤንያ ሆይ ፥ ኢየሱስ ክርስቶስ ይፈውስሃል ፤ ተነሣ ለራስህም አንጥፍ አለው። ወዲያውም ተነሣ። በልዳና በሰሮናም የሚኖሩ ሁሉ እርሱን አይተው ወደ ጌታ ዘወር አሉ።* (ሐዋ.፱፡፴፪-፴፭)

**ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ** ታላላቅ ተአምራቶችና ድንቅ ስለማድረጉ፦ እግዚአብሔርም በጳውሎስ እጅ የሚያስገርም ተአምራት ያደርግ ነበር ፤ ስለዚህም ከአካሉ ጨርቅ ወይም ልብስ ወደ ድውዮች ይወስዱ ነበር ፥ ደዌያቸውም ይለቃቸው ነበር ክፉዎች መናፍስትም ይወጡ ነበር። (ሐዋ.፲፱፡፲፩-፲፪)

Copyright © 2009 Debre Selam Medhanealem Ethiopian Orthodox Tewahedo Church 4401 Minnehaha Avenue South Minneapolis, Minnesota 55406 Tel. (612) 721-1222 (U.S.A)

## ፯- ሁለቱም ሙታንን አሥነስተዋል፦

**ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ** ጣቢታ የተባለችውን ብላቴና ስለማሥነሳቱ፦ በኢዮጴም ጣቢታ የሚሉአት አንዲት ደቀ መዝሙር ነበረች ፤ ትርጓሜውም ዶርቃ ማለት ነው ፣ እርስዋም መልካም ነገር የሞላባት ምጽዋትም የምታደርግ ነበረች። በዚያም ወራት ታመመችና ሞተች ፣ አጥበውም በሰገነት አኖሩአት። ልዳም ለኢዮጴ ቅርብ ናትና ደቀ መዛሙርት ጴጥሮስ በዚያ እንዳለ ሰምተው ፤ ወደ እነርሱ ከመምጣት እንዳይዘገይ እየለመኑ ሁለት ሰዎች ወደ እርሱ ላኩ። ጴጥሮስም ተነሥቶ ከእነርሱ ጋር መጣ ፣ በደረሰም ጊዜ በሰገነት አወጡት መበለቶችም ሁሉ እያለቀሱ ዶርቃ ከእነርሱ ጋር ሳለች ያደረገቻቸውን ቀሚሶችንና ልብሶችን ሁሉ እያሳዩት በፊቱ ቆሙ። ጴጥሮስም ሁሉን ወደ ውጭ አስወጥቶ ተንበርክኮም ጸለየ ፤ ወደ ሬሳውም ዘወር ብሎ። <u>ጣቢታ ሆይ ፤ ተነሺ አላት። እርስዋም ዓይኖችዋን ከፈተች ጴጥሮስንም ባየች ጊዜ ተቀመጠች። እጁንም ለእርስዋ ሰጥቶ አስነሣት ፣ ቅዱሳንንና መበለቶችንም ጠራ ሕያውም ሆና በፊታቸው አቆማት።</u> (ሐዋ.፱፡፴፮-፵፩)

**ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ** አውጤኪስን ከሞት ስለማሥነሳቱ፦ ከሳምንቱም በመጀመሪያ ቀን እንጀራ ለመቁረስ ተሰብስበን ሳለን ፤ ጳውሎስ በነገው ሊሄድ ስላሰበ ከእነርሱ ጋር ይነጋገር ነበር ፤ እስከ መንፈቀ ሌሊትም ነገሩን አስረዘመ። ተሰብስበንም በነበርንበት ሰገነት እጅግ መብራት ነበረ። አውጤኪስ የሚሉትም አንድ ጎበዝ በመስኮት ተቀምጦ ታላቅ እንቅልፍ አንቀላፍቶ ነበር ፣ ጳውሎስም ነገርን ባስረዘመ ጊዜ እንቅልፍ ከብዶት ከሦስተኛው ደርብ ወደ ታች ወደቀ ፤ ሞቶም አነሡት። ጳውሎስም ወርዶ በላዩ ወደቀ ፤ አቅፎም። ነፍሱ አለችበትና አትንጫጩ አላቸው። ወጥቶም እንጀራ ቆርሶም በላ ፣ ብዙ ጊዜም እስኪነጋ ድረስ ተነጋገረ እንዲህም ሄደ። ብላቴናውንም ደኅና ሆኖ ወሰዱት እጅግም ተጽናኑ። (ሐዋ.፳፡፯-፲፪)

## ፰- ሁለቱም እሳታዊ ኃይል ፣ መንፈሳዊ ቅናት ፣ የሥራ ትጋት ፣ የስብከት ተሰጥዖና የአገልግሎት ጽናት ነበራቸው፦

**ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ** የጌታን ነገር አብዝቶ እየሰበከ ለሕዝቡ ሁሉ ንስሐ ገብተው በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተጠምቀው እንዲድኑ መልእክትን በማስተላለፉ ብዙዎች ቃሉን ሰምተው እንደተገበሩት ተገልጿል፦ <u>*የተስፋው ቃል ለእናንተና ለልጆቻችሁ ጌታ አምላካችንም ወደ እርሱ ለሚጠራቸው በሩቅ ላሉ ሁሉ ነውና አላቸው። በብዙ ሌላ ቃልም መሰከረና። ከዚህ ጠማማ ትውልድ ዳኑ ብሎ መከራቸው። ቃሉንም የተቀበሉ ተጠመቁ ፤ በዚያም ቀን ሦስት ሺህ የሚያህል ነፍስ ተጨመሩ ፣*</u> (ሐዋ.፪፡፲፬-፵፩)

በሌላ ሥፍራም **ቅዱስ ጴጥሮስ** ለቆርነሌዎስንና ለቤተሰቡ የጌታን ነገር አብዝቶ እንደሰበከላቸውና መንፈስ ቅዱስን እንደተቀበሉ ተገልጿል። በእርሱ የሚያምን ሁሉ በስሙ የኃጢአቱን ስርየት እንዲቀበል ነቢያት ሁሉ ይመሰክሩለታል። ጴጥሮስ ይህን ነገር ገና ሲናገር ቃሉን በሰሙት ሁሉ ላይ መንፈስ ቅዱስ ወረደ። ከጴጥሮስም ጋር የመጡት ሁሉ ከተገረዙት ወገን የሆኑ ምዕመናን በአሕዛብ ላይ ደግሞ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ ስለ ፈሰሰ ተገረሙ ፣ (ሐዋ.፲፡፵፬-፵፰)

**ቅዱስ ጴጥሮስ** በስብከቱም ብዙዎችን እንዳነጸና ስለ ክርስቶስ እንደመሰከረ ከመልእክቱ ይህን ቃል እናገኛለን፦ <u>*ለእውነት እየታዘዛችሁ ግብዝነት ለሌለበት ለወንድማማች መዋደድ ነፍሳችሁን አንጽታችሁ እርስ በርሳችሁ ከልባችሁ አጥብቃችሁ ተዋደዱ። ዳግመኛ የተወለዳችሁት ከሚጠፋ ዘር አይደለም ፤ በሕያውና ለዘላለም በሚኖር በእግዚአብሔር ቃል ከማይጠፋ ዘር ነው እንጂ። ሥጋ ሁሉ እንደ ሣር ክብሩም ሁሉ እንደ ሣር አበባ ነውና ፣ ሣሩ ይጠወልጋል አበባውም ይረግፋል ፣ የጌታ ቃል ግን ለዘላለም ይኖራል። በወንጌልም የተሰበከላችሁ ቃል ይህ ነው።*</u> (፩ጴጥ.፩፡፳፪-፳፭)

Copyright © 2009 Debre Selam Medhanealem Ethiopian Orthodox Tewahedo Church 4401 Minnehaha Avenue South Minneapolis, Minnesota 55406 Tel. (612) 721-1222 (U.S.A)

**ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ** ስለተመረጠ እና ስለተደነቀ አገልግሎቱ ቅዱስ መጽሐፍ እንዲህ ሲል ያስረዳል፦ *ሳውል ግን እየበረታ ሄደ ፥ በደማስቆም ለተቀመጡት አይሁድ ይህ ክርስቶስ እንደ ሆነ አስረድቶ መልስ ያሳጣቸው ነበር።....በይሁዳም ሁሉና በገሊላ በሰማርያም የነበሩት አብያተ ክርስቲያናት በሰላም ኖሩ ታነጹም ፤ በእግዚአብሔርም ፍርሃትና በመንፈስ ቅዱስ መጽናናት እየሄዱ ይበዙ ነበር።* (ሐዋ. ፱፡፳፪ እና ፴፩)

## ፱- ሁለቱም ስለጀመሩት የወንጌል አደራ ብርቱዎችና ደፋሮች ነበሩ፦

**ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ** ስለ አይሁድ ማስፈራራትና ዛቻ ሳይበገር የወንጌልን ቃል በሙላት ይሰብክ ነበር፦ ጴጥሮስና ሐዋርያትም መልሰው አሉ። ከሰው ይልቅ ለእግዚአብሔር ልንታዘዝ ይገባል። (ሐዋ.፭፡፳፱) ከዚህም ባሻገር ይዘልፍና ይገስጻቸው ነበር፦ የአብርሃምና የይስሐቅ የያዕቆብም አምላክ ፥ የአባቶቻችን አምላክ ፥ እናንተ አሳልፋችሁ የሰጣችሁትንና ሊፈታው ቈርጦ ሳለ በጲላጦስ ፊት የካዳችሁትን ብላቴናውን ኢየሱስን አከበረው። እናንተ ግን ቅዱሱን ጻድቁንም ክዳችሁ ነፍሰ ገዳዩን ሰው ይሰጣችሁ ዘንድ ለመናችሁ ፥ የሕይወትንም ራስ ገደላችሁት ፤ እርሱን ግን እግዚአብሔር ከሙታን አስነሣው ፥ ለዚህም ነገር እኛ ምስክሮች ነን። (ሐዋ.፫፡፲፫-፲፭)

**ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ** ስለ ወንጌልና ስለ ክርስቶስ ጉዳይ በድፍረት ከአገረ ገዥዎች ጋር ይነጋገር ነበር፦ ከጥቂት ቀንም በኋላ ፊልክስ አይሁዳዊት ከነበረች ድሩሲላ ከሚሉአት ከሚስቱ ጋር መጥቶ ጳውሎስን አስመጣ ፥ በኢየሱስ ክርስቶስም ስለ ማመን የሚናገረውን ሰማው። እርሱም ስለ ጽድቅና ራስን ስለ መግዛት ስለሚመጣውም ኵነኔ ሲነጋገር ሳለ ፥ ፊልክስ ፈርቶ። አሁንስ ሂድ ፥ በተመቸኝም ጊዜ ልኬ አስጠራሃለሁ ብሎ መለሰለት። (ሐዋ.፳፬፡፳፭)

ቅዱስ ጳውሎስም ንጉሥ አግሪጳን እንዴት እንዳነጋገረና የጳውሎስንም ንግግር ሰምተው ለእስር የሚያበቃ አንዳች ነገር አላደረገም እስኪሉ ድረስ መገረማቸውን፦ ንጉሥ አግሪጳ ሆይ ፥ ነቢያትን ታምናለህን? እንድታምናቸው አውቃለሁ። አግሪጳም ጳውሎስን። በጥቂት ክርስቲያን ልታደርገኝ ትወዳለህ አለው። ጳውሎስም። በጥቂት ቢሆን ወይም በብዙ አንተ ብቻ አይደለህም ነገር ግን ዛሬ የሚሰሙኝ ሁሉ ደግሞ ከዚህ እስራቴ በቀር እንደ እኔ ይሆኑ ዘንድ ወደ እግዚአብሔር እለምናለሁ አለው። (ሐዋ.፳፮፡፳፯-፳፱)

ቅዱስ ጳውሎስ ስለደረሰበት መከራ እንዴት አድርጎ በድፍረት ከመቶ አለቃው ጋር እንደተነጋገረና የመቶ አለቃውም በጉዳዩ እንዴት እንደተጨነቀ እንዲህ ሲል ተጽፏል፦ *በጠፍርም በገተሩት ጊዜ ጳውሎስ በአጠገቡ የቆመውን የመቶ አለቃ። የሮሜን ሰው ያለ ፍርድ ትገርፉ ዘንድ ተፈቅዶላችኋልን? አለው። የመቶ አለቃውም በሰማ ጊዜ ወደ ሻለቃው ቀርቦ። ይህ ሰው ሮማዊ ነውና ታደርገው ዘንድ ካለህ ተጠበቅ ብሎ ነገረው። የሻለቃውም ቀርቦ። አንተ ሮማዊ ነህን? ንገረኝ አለው ፤ እርሱም። አዎን አለ። የሻለቃውም መልሶ። እኔ ይህን ዜግነት በብዙ ገንዘብ አገኘሁት አለ። ጳውሎስም። እኔ ግን በእርስዋ ተወለድሁ አለ። ስለዚህም ሊመረምሩት ያሰቡት ከእርሱ ወዲያው ተለዩ ፤ የሻለቃውም ደግሞ ሮማዊ መሆኑን ባወቀ ጊዜ ፈራ ፥ አሳስሮት ነበርና።* (ሐዋ.፳፪፡፳፭-፳፱)

በፊልክስ ቦታ ተተክቶ የገባ ፊስጦስ ከተባለ አለቃ ጋር እንዴት ቅዱስ ጳውሎስ እንደተነጋገረ፦ ፊስጦስ ግን አይሁድን ደስ ያሰኝ ዘንድ ወዶ ጳውሎስን። ወደ ኢየሩሳሌም ወጥተህ ስለዚህ ነገር ከዚያው በፊቴ ትፋረድ ዘንድ ትወዳለህን? ብሎ መለሰለት። ጳውሎስ ግን። እፋረድበት ዘንድ በሚገባኝ በቄሳር ፍርድ ወንበር ፊት ቆሜአለሁ። አንተው ደግሞ ፈጽመህ እንደምታውቅ አይሁድን ምንም አልበደልሁም። እንግዲህ በድዬ ወይም ሞት የሚገባውን ነገር አድርጌ እንደ ሆነ ከሞት ልዳን አልልም ፤ እነዚህ የሚከሱኝ ክስ ከንቱ እንደሆነ ግን ለእነርሱ አሳልፎ ይሰጠኝ ዘንድ ማንም አይችልም ፤ ወደ ቄሳር ይግባኝ ብዬአለሁ አለ። በዚያን ጊዜ ፊስጦስ ከአማካሪዎቹ ጋር ተማክሮ። ወደ ቄሳር ይግባኝ ብለሃል ፤ ወደ ቄሳር ትሄዳለህ ብሎ መለሰለት። (ሐዋ.፳፭፡፲-፲፪)

Copyright © 2009 Debre Selam Medhanealem Ethiopian Orthodox Tewahedo Church 4401 Minnehaha Avenue South Minneapolis, Minnesota 55406 Tel. (612) 721-1222 (U.S.A)

## ፲- ሁለቱም በደለኞችን በመቅጣት ቀጥተኛ አቋም ነበራቸው፡-

**ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ** አናንያ እና ሰጲራ ላይ የፈጸመው ቅጣት እና ያስከተለው ሃይማኖታዊ ፍርሃት እንዲህ ሲል ተገልጿል። ባልና ሚስቱ ተስማምተው ከሸጡት መሬት ላይ ግማሹን ገንዘብ ደብቀው በማቅረባቸው የቅዱስ ጴጥሮስ ፍርድ ይህን ይመስል ነበር፡- *ሳትሸጠው የአንተ አልነበረምን? ከሸጥኸውስ በኋላ በሥልጣንህ አልነበረምን? ይህን ነገር ስለ ምን በልብህ አሰብህ? እግዚአብሔርን እንጂ ሰውን አልዋሸህም* አለው። ሐናንያም ይህን ቃል ሰምቶ ወደቀ ሞተም ፤ በሰሙትም ሁሉ ላይ ታላቅ ፍርሃት ሆነ። ጐበዞችም ተነሥተው ከፈኑት አውጥተውም ቀበሩት። (ሐዋ.፭፡፩-፮)

የአናንያ ባለቤትም ሰጲራ በድርጊቱ ከባልዋ ጋር ፍጹም ተባባሪ በመሆንዋ ቅዱስ ጴጥሮስ ተመሳሳይ ፍርድ እንዲህ ሲል ሰጥቷል፡- *የጌታን መንፈስ ትፈታተኑ ዘንድ ስለ ምን ተስማማችሁ? እነሆ ፥ ባልሽን የቀበሩት ሰዎች እግር በደጅ ነው አንቺንም ያወጡሻል* አላት። ያን ጊዜም በእግሩ አጠገብ ወደቀች ሞተችም ፤ ጐበዞችም ሲገቡ ሞታ አገኙአት አውጥተውም በባልዋ አጠገብ ቀበሩአት። በቤተ ክርስቲያን ሁሉና ይህንም በሰሙ ሁሉ ላይ ታላቅ ፍርሃት ሆነ። (ሐዋ.፭፡፯-፲፩)

የመንፈስ ቅዱስ ስጦታን በገንዘብ መግዛት የፈለገውን ሰው ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ እንዴት አድርጎ እንደገሰጸውና ወደ ንስሐ መንገድ እንዲሄድ እንዳዘዘው እንዲህ ሲል በመጽሐፍ ተጽፏል፡- *ሲሞንም በሐዋርያት እጅ መጫን መንፈስ ቅዱስ እንዲሰጥ ባየ ጊዜ ፥ ገንዘብ አመጣላቸውና። እጄን የምጭንበት ሁሉ መንፈስ ቅዱስን ይቀበል ዘንድ ለእኔ ደግሞ ይህን ሥልጣን ስጡኝ አለ። ጴጥሮስ ግን እንዲህ አለው። የእግዚአብሔርን ስጦታ በገንዘብ እንድታገኝ አስበሃልና ብርህ ከአንተ ጋር ይጥፋ። ልብህ በእግዚአብሔር ፊት የቀና አይደለምና ከዚህ ነገር ዕድል ወይም ፈንታ የለህም። እንግዲህ ስለዚህ ክፋትህ ንስሐ ግባ ፥* ምናልባትም የልብህን አሳብ ይቅር ይልህ እንደ ሆነ ወደ እግዚአብሔር ለምን ፤ (ሐዋ.፰፡፲፰-፳፪)

**ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ** በቆሮንቶስ ሕዝብ መካከል ስላለው የኃጢአት ሥራ በተለይም ስለ ዝሙት መጥፎነት አውስቶ ከመካከላችሁ ከእናቱ ጋር በመተኛት (ዝሙት በመፈጸም አሳዛኝ ነውርን ያደረገውን ሰው መቅጣት እና ማግለል እንደሚገባ ሲያስተምር፡- *እኔ ምንም እንኳ በሥጋ ከእናንተ ጋር ባልሆን ፥ በመንፈስ ከእናንተ ጋር ነኝ ፥ ከእናንተም ጋር እንዳለሁ ሆኜ ይህን እንደዚህ በሠራው ላይ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም አሁን ፈርጄበታለሁ ፤ እናንተና መንፈሴም ከጌታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ ኃይል ጋር ተሰብስበን ፥ መንፈሱ በጌታ በኢየሱስ ቀን ትድን ዘንድ እንደዚህ ያለው ለሥጋው ጥፋት ለሰይጣን እንዲሰጥ ፍርዴ ነው።*(ሐዋ.፭፡፫-፭)

አሁን ግን ወንድሞች ከሚባሉት አንዱ ሴሰኛ ወይም ገንዘብን የሚመኝ ወይም ጣዖትን የሚያመልክ ወይም ተሳዳቢ ወይም ሰካር ወይም ነጣቂ ቢሆን ከእርሱ ጋር እንዳትተባበሩ እጽፍላችኋለሁ ፤ እንደነዚህ ካለው ጋር መብል እንኳን አትብሉ። በውጭ ባሉ ሰዎች ላይ መፍረድ ምን አግዶኝ? በውስጥ ባሉ ሰዎች ላይ እናንተ አትፈርዱምን? *በውጭ ባሉቱ ግን እግዚአብሔር ይፈርድባቸዋል። ክፉውን ከመካከላችሁ አውጡት።* (ሐዋ.፭፡፲፪-፲፫)

**ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ** ኤልማስ የተባለውን ሐሰተኛ ነቢይና ጠንቋይ የእግዚአብሔር ቃል እንዳይደመጥ ያደርግ ስለነበረው ሁኔታ እንዴት እንደተቃወመውና ድርጊቱንም በማውገዝ የጌታ እጅ በአንተ ላይ ናት ቅጣትን ትቀበላለህ ብሎ ስለመናገሩ፡- *ጳውሎስ የተባለው ሳውል ግን መንፈስ ቅዱስን ተሞልቶ ትኵር ብሎ ሲመለከተው። አንተ ተንኰል ሁሉ ክፋትም ሁሉ የሞላብህ ፥ የዲያብሎስ ልጅ ፥ የጽድቅም ሁሉ ጠላት ፥ የቀናውን የጌታን መንገድ ከማጣመም አታርፍምን? አሁንም ፥ እነሆ ፥ የጌታ እጅ በአንተ ላይ ናት ፥ ዕውርም ትሆናለህ እስከ ጊዜውም ፀሐይን አታይም አለው። ያን ጊዜም ጭጋግና ጨለማ ወደቀበት ፥ በእጁም የሚመራውን እየዞረ ፈለገ።* (ሐዋ.፲፫፡፰-፲፪)

Copyright © 2009 Debre Selam Medhanealem Ethiopian Orthodox Tewahedo Church 4401 Minnehaha Avenue South Minneapolis, Minnesota 55406 Tel. (612) 721-1222 (U.S.A)

## ፲፩- ሁለቱም እጅግ በጣም ትሁታን ነበሩ፡-

**ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ** ሌሊቱን ሙሉ ደክሞ ዓሣ ማጥመድ ሳይችል ቀርቶ ጌታ መረቡን በስተቀኝ በኩል ጣሉት ካለ በኋላ እጅግ ብዙ አሳዎች በመገኘታቸው ቅዱስ ጴጥሮስ ጌታን እንዲህ ነበር ያለው፡- *ስምዖን ጴጥሮስ ግን ባየ ጊዜ በኢየሱስ ጉልበት ላይ ወድቆ። ጌታ ሆይ ፥ እኔ ኃጢአተኛ ነኝና ከኔ ተለይ አለው።* ስላጠመዱት ዓሣ እርሱ ከእርሱ ጋርም የነበሩ ሁሉ ተደንቀዋልና ፥(ሉቃ.፳፪፡፴፫-፴፬)በትውፊትም እንደምንረዳው ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ በሰማእትነት ሲያልፍ ጌታ እንደተሰቀለው ሳይሆን እኔ ቁልቁል መሰቀል ይገባኛል በማለት በሞቱ ጊዜ እንኳን ሳይቀር ትኅትናውን ማሳየቱ ነው።

**ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ** ምንም እንኳን በብዙ ድካም ወንጌልን እየሰበከ እና ድንቅ ተአምራትን እያደረገ ቢኖርም ለመንፈስ ልጁ ለጢሞቴዎስ እንዲህ ሲል መልእክት አስተላልፎለታል፡- አስቀድሞ ተሳዳቢና አሳዳጅ አንገላችም ምንም ብሆን ፥ ይህን አደረገልኝ ፤ ነገር ግን ሳላውቅ ባለማመን ስላደረግሁት ምህረትን አገኘሁ ፥ (፩ጢሞ.፩፡፲፫)

## ፲፪- ሁለቱም ለብዙ ፈተናና ስደት ተጋልጠዋል፡-

እኛም ለዚህ ነገር ምስክሮች ነን ፥ ደግሞም እግዚአብሔር ለሚታዘዙት የሰጠው መንፈስ ቅዱስ ምስክር ነው። እነርሱም ሲሰሙ በጣም ተቈጡ ሊገድሉአቸውም አሰቡ። ነገር ግን በሕዝብ ሁሉ ዘንድ የከበረ የሕግ መምህር ገማልያል የሚሉት አንድ ፈሪሳዊ በሸንጎ ተነሥቶ ሐዋርያትን ጥቂት ፈቀቅ እንዲያደርጉአቸው አዘዘ ፥ እንዲህም አላቸው። የእስራኤል ሰዎች ሆይ ፥ ስለ እነዚህ ሰዎች ምን እንደምታደርጉ ለራሳችሁ ተጠንቀቁ። ከዚህ ወራት አስቀድሞ ቴዎዳስ። እኔ ታላቅ ነኝ ብሎ ተነሥቶ ነበርና ፥ አራት መቶ የሚያህሉ ሰዎችም ከእርሱ ጋር ተባበሩ ፤ እርሱም ጠፋ የሰሙትም ሁሉ ተበተኑ እንደ ምናምንም ሆኑ። ከዚህ በኋላ ሰዎች በተጻፉበት ዘመን የገሊላው ይሁዳ ተነሣ ብዙ ሰዎችንም አሸፍቶ አስከተለ ፤ እርሱም ጠፋ የሰሙትም ሁሉ ተበታተኑ። አሁንም እላችኋለሁ። ከእነዚህ ሰዎች ተለዩ ተዉአቸውም ፤ ይህ አሳብ ወይም ይህ ሥራ ከሰው እንደ ሆነ ይጠፋልና ፤ ከእግዚአብሔር እንደ ሆነ ግን ታጠፉአቸው ዘንድ አይቻላችሁም ፥ በእርግጥ ከእግዚአብሔር ጋር ስትጣሉ ምናልባት እንዳትገኙ። ሰሙትም ፥ ሐዋርያትንም ወደ እነርሱ ጠርተው ገረፉአቸው ፥ በኢየሱስም ስም እንዳይናገሩ አዝዘው ፈቱአቸው። (ሐዋ.፭፡፴፬-፵)

**ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ** እጅግ መከራ እንደደረሰበት እና ያዕቆብን በሰይፍ የገደለ ሔሮድስ ቅዱስ ጴጥሮስንም እንዳስያዘው መጽሐፍ ሲገልጽልን፡- አይሁድንም ደስ እንዳሰኛቸው አይቶ ጨምሮ ጴጥሮስን ደግሞ ያዘው። የቂጣ በዓልም ወራት ነበረ። በያዘውም ጊዜ ወደ ወኅኒ አገባው ከፋሲካም በኋላ ወደ ሕዝብ ያወጣው ዘንድ አስቦ እያንዳንዱ አራት ወታደሮች ሆነው እንዲጠብቁት ለአራት ጭፍራ ክፍል አሳልፎ ሰጠው። (ሐዋ.፲፪፡፫-፬)

በሌላ ቦታም ቅዱስ ጴጥሮስ ስለመከራው ሲናገር፡- *በሁሉ እንገፋለን እንጂ አንጨነቅም ፤ እናመነታለን እንጂ ተስፋ አንቆርጥም ፤ እንሰደዳለን እንጂ አንጣልም ፤ እንወድቃለን እንጂ አንጠፋም ፤ የኢየሱስ ሕይወት ደግሞ በሥጋችን ይገለጥ ዘንድ ሁልጊዜ የኢየሱስን መሞት በሥጋችን ተሸክመን እንዞራለን። የኢየሱስ ሕይወት ደግሞ በሚሞት ሥጋችን ይገለጥ ዘንድ እኛ ሕያዋን የሆንን ከኢየሱስ የተነሣ ዘወትር ለሞት አልፈን እንሰጣለንና።* (፪ቆሮ.፬፡፰-፲፩)

**ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ** እጅግ ብዙ ፈተና ፣ እስር ፤ ስቃይ ፤ መከራ እና መገፋት እንደደረሰበት አገልግሎትን በተመለከተ በቅዱስ መጽሐፍ ላይ ባሰፈረልን መልእክት እንዲህ ሲል አስተላልፏል፡- አገልግሎታችንም እንዳይነቀፍ በአንዳች ነገር ማሰናከያ ከቶ አንሰጥም። ነገር ግን በሁሉ እንደ እግዚአብሔር አገልጋዮች ራሳችንን እናማጥናለን ፤ በብዙ መጽናት ፥ በመከራ ፥ በችግር ፥ በጭንቀት ፥ በመገረፍ ፥ በወኅኒ ፥ በሁከት ፥ በድካም ፥ እንቅልፍ በማጣት ፥ (፪ቆሮ.፮፡፫-፭)

Copyright © 2009 Debre Selam Medhanealem Ethiopian Orthodox Tewahedo Church 4401 Minnehaha Avenue South Minneapolis, Minnesota 55406 Tel. (612) 721-1222 (U.S.A)

በሌላ ሥፍራም ስለደረሰበት ብዙ መከራ እንዲህ ሲል ወደ ቆሮንቶስ ሰዎች መልእክቱን አስተላልፏል፦ ደካሞች መስለን እንደ ነበርን በውርደት እላለሁ። ነገር ግን በሞኝነት እላለሁ ፤ ማንም በሚደፍርበት እኔ ደግሞ እደፍርበታለሁ። ዕብራውያን ናቸውን? እኔ ደግሞ ነኝ። የእስራኤል ወገን ናቸውን? እኔ ደግሞ ነኝ። የአብርሃም ዘር ናቸውን? እኔ ደግሞ ነኝ። የክርስቶስ አገልጋዮች ናቸውን? እንደ እብድ ሰው እላለሁ ፤ እኔ እበልጣለሁ ፤ በድካም አብዝቼ ፥ በመገረፍ አብዝቼ ፥ በመታሰር አትርፌ ፥ በመሞት ብዙ ጊዜ ሆንሁ። አይሁድ አንድ ሲጎድል አርባ ግርፋት አምስት ጊዜ ገረፉኝ። ሦስት ጊዜ በበትር ተመታሁ ፤ አንድ ጊዜ በድንጋይ ተወገርሁ ፤ መርከቤ ሦስት ጊዜ ተሰበረ ፤ ሌሊትና ቀን በባሕር ውስጥ ኖርሁ። ብዙ ጊዜ በመንገድ ሄድሁ ፤ በወንዝ ፍርሃት ፥ በወንበዴዎች ፍርሃት ፥ በወገኔ በኩል ፍርሃት ፥ በአሕዛብ በኩል ፍርሃት ፥ በከተማ ፍርሃት ፥ በምድረ በዳ ፍርሃት ፥ በባሕር ፍርሃት ፥ በውሸተኞች ወንድሞች በኩል ፍርሃት ነበረብኝ ፤ በድካምና በጥረት ብዙ ጊዜም እንቅልፍ በማጣት ፥ በራብና በጥም ብዙ ጊዜም በመጦም ፥ በብርድና በራቁትነት ነበርሁ። የቀረውንም ነገር ሳልቆጥር ፥ ዕለት ዕለት የሚከብድብኝ የአብያተ ክርስቲያናት ሁሉ አሳብ ነው። ፪ቆሮ.፲፩፥፳፩-፳፰

## ፲፫- ሁለቱም የሰማዕትነት አክሊል አግኝተዋል፦

**ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ** በስልሣ ሰባት ዓ.ም. በኔሮን ቄሣር እጅ ቁልቁል ተሰቅሎ ሕይወቱን አጥቷል (ሰማዕትነትን ተቀብሏል)።

**ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ** በስልሣ ሰባት ዓ.ም. በኔሮን ቄሣር እጅ አንገቱን ተቆርጦ ሕይወቱን አጥቷል (ሰማዕትነትን ተቀብሏል)።

## ስለ ሁለቱ ቅዱሳን ማጠቃለያ፦

## ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ፦

- የዮና ልጅ ስምዖን ፤ ኬፋ ፤ ጴጥሮስ በሚባሉ ሦስት መጠሪያ ስሞች ይታወቃል።
- እንድርያስ የተባለ ዓሣ አጥማጅ ወንድም ነበረው። ክርስቶስን መጀመሪያ ያወቀው ወንድሙ እንድርያስ ነው። ከዮሐንስ ዘንድ ሰምተው ከተከተሉት ከሁለቱ አንዱ የስምዖን ጴጥሮስ ወንድም እንድርያስ ነበረ። እርሱ አስቀድሞ የራሱን ወንድም ስምዖንን አገኘውና። መሢሕን አግኝተናል አለው ፤ ትርጓሜውም ክርስቶስ ማለት ነው። ወደ ኢየሱስም አመጣው። ኢየሱስም ተመልክቶ። አንተ የዮና ልጅ ስምዖን ነህ ፤ አንተ ኬፋ ትባላለህ አለው ፤ ትርጓሜው ጴጥሮስ ማለት ነው። ዮሐ.፩፥፵፩-፵፫
- በሐዋርያት የስም ዝርዝር ውስጥ መጀመሪያ የተገለጸው ጴጥሮስ ነው። (ማቴ.፲፥፪)
- ለጌታ እጅግ ቅርብ ከነበሩ ሦስት ሐዋርያት መካከል ማለትም ከያዕቆብ እና ከዮሐንስ ጋር አንዱ ነው። መጽሐፍ ቅዱስም እንዲህ ይላል፦
    - ከስድስት ቀንም በኋላ ኢየሱስ ጴጥሮስንና ያዕቆብን ወንድሙንም ዮሐንስን ይዞ ወደ ረጅም ተራራ ብቻቸውን አወጣቸው። በፊታቸውም ተለወጠ ፥ ፊቱም እንደ ፀሐይ በራ ፥ ልብሱም እንደ ብርሃን ነጭ ሆነ። እነሆም ፥ ሙሴና ኤልያስ ከእርሱ ጋር ሲነጋገሩ ታዩአቸው። ማቴ.፲፯፥፩-፪
    - የኢያኢሮስን ልጅ ከሞት ባስነሣ ጊዜ፦ እርሱም ገና ሲናገር ከምኵራብ አለቃው ቤት ዘንድ የመጡት። ልጅህ ሞታለች ፤ ስለ ምን መምህሩን አሁን ታደክመዋለህ? አሉት። ኢየሱስ ግን የተናገሩትን ቃል አድምጦ ለምኵራቡ አለቃ። እመን ብቻ እንጂ አትፍራ አለው። ከጴጥሮስም ከያዕቆብም ከያዕቆብም ወንድም ከዮሐንስ በቀር ማንም እንዲከተለው አልፈቀደም። ማር. ፭፥፴፭-፴፯

- ❖ ጌታም በጌቴሴማኒ ደቀ መዛሙርቱን፦ ወዲያ ሄጄ ስጸልይ ሳለ በዚህ ተቀመጡ አላቸው። ጴጥሮስንም ሁለቱንም የዘብዴዎስን ልጆች ወስዶ ሊያዝን ሊተክዝም ጀመር። ነፍሴ እስከ ሞት ድረስ እጅግ አዘነች ፤ በዚህ ቆዩ ከእኔም ጋር ትጉ አላቸው። ማቴ.፳፮፡፴፮-፴፰

- ➢ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስም ስለ ቅዱስ ጴጥሮስ ሲመሰክር፦ ደግሞ የተሰጠኝን ጸጋ አውቀው ፥ አዕማድ መስለው የሚታዩ ያዕቆብና ኬፋ ዮሐንስም እኛ ወደ አሕዛብ እነርሱም ወደ ተገረዙት ይሄዱ ዘንድ ለእኔና ለበርናባስ ቀኝ እጃቸውን ሰጡን ፤ ገላ.፪፡፱
- ➢ ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ ጌታን እጅግ አድርጎ ይወደው ነበር። መጽሐፉም እንዲህ ይላል፦

  - ❖ ከዚህም የተነሣ ከደቀ መዛሙርቱ ብዙዎች ወደ ኋላ ተመለሱ ፤ ወደ ፊትም ከእርሱ ጋር አልሄዱም። ኢየሱስም ለአሥራ ሁለቱ። እናንተ ደግሞ ልትሄዱ ትወዳላችሁን? አለ። ስምዖን ጴጥሮስ። ጌታ ሆይ ፥ ወደ ማን እንሄዳለን? አንተ የዘላለም ሕይወት ቃል አለህ ፤ ዮሐ.፮፡፷፮-፷፰
  - ❖ ሁሉም በአንተ ቢሰናከሉ እኔ ከቶ አልሰናከልም ...ከአንተ ጋር መሞት እንኳ የሚያስፈልገኝ ቢሆን ፥ ከቶ አልክድህም አለው። ማቴ.፳፮፡፴፫-፴፭
  - ❖ ጌታ ሆይ ፥ ወደ ወኅኒም ወደ ሞትም ከአንተ ጋር ለመሄድ የተዘጋጀሁ ነኝ አለው።ሉቃ.፳፪፡፴፫

- ➢ ሦስት ሺህ ሰዎች በትምህርቱ አምነው መጠመቃቸው (ሐዋ. ፪፡፵፩)
- ➢ ሽባውን ሰው ስለመፈወሱ፦ እርሱም አንድ ነገር ከእነርሱ እንዲቀበል ሲጠብቅ ወደ እነርሱ ተመለከተ። ጴጥሮስ ግን ብርና ወርቅ የለኝም ፤ ይህን ያለኝን ግን እሰጥሃለሁ ፤ በናዝሬቱ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተነሣና ተመላለስ አለው። በቀኝ እጁም ይዞ አስነሣው በዚያን ጊዜም እግሩና ቍርጭምጭምቱ ጸና ፥(ሐዋ.፫፡፮-፯)

## ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ

- ➢ ከሁሉ አብልጦ በማገልገል በረታ፦ ነገር ግን በእግዚአብሔር ጸጋ የሆንሁ እኔ ነኝ ፤ ለእኔም የተሰጠኝ ጸጋው ከንቱ አልነበረም ከሁላቸው ይልቅ ግን ደከምሁ ፥ ዳሩ ግን ከእኔ ጋር ያለው የእግዚአብሔር ጸጋ ነው እንጂ እኔ አይደለሁም። ፩ቆሮ.፲፭፡፲

- ➢ ብዙ መገለጥ እና ስጦታ ተሰጠው ወደ ሰማይም ተነጠቀ፦ ትምክህት የሚያስፈልግ ነው ፤ አይጠቅምም ነገር ግን ከጌታ ወዳለው ራእይና መገለጥ እመጣለሁ። ሰውን በክርስቶስ አውቃለሁ ፥ በሥጋ እንደ ሆነ አላውቅም ወይም ከሥጋ ውጭ እንደ ሆነ አላውቅም ፥ እግዚአብሔር ያውቃል ፤ እንዲህ ያለው ሰው ከአሥራ አራት ዓመት በፊት እስከ ሦስተኛው ሰማይ ድረስ ተነጠቀ። እንዲህ ያለውንም ሰው አውቃለሁ ፥ በሥጋ እንደ ሆነ ወይም ያለ ሥጋ እንደ ሆነ አላውቅም ፥ እግዚአብሔር ያውቃል ፤ ወደ ገነት ተነጠቀ ፥ ሰውም ሊናገር የማይገባውን የማይነገረውን ቃል ሰማ። እንደዚህ ስላለው እመካለሁ ፥ ስለ ራሴ ግን ከድካሜ በቀር አልመካም።

  ልመካ ብወድስ ሞኝ አልሆንም ፥ እውነትን እላለሁና ፤ ነገር ግን ማንም ከሚያይ ከእኔም ከሚሰማ የምበልጥ አድርጎ እንዳይቆጥረኝ ትቼአለሁ። ስለዚህም በመገለጥ ታላቅነት እንዳልታበይ የሥጋዬ መውጊያ ፥ እርሱም የሚጎስመኝ የሰይጣን መልእክተኛ ተሰጠኝ ፤ ይኸውም እንዳልታበይ ነው። ስለዚህ ነገር ከእኔ እንዲለይ ሦስት ጊዜ ጌታን ለመንሁ። እርሱም። ጸጋዬ ይበቃሃል ፥ ኃይሌ በድካም ይፈጸማልና አለኝ። እንግዲህ የክርስቶስ ኃይል ያድርብኝ ዘንድ በብዙ ደስታ በድካሜ ልመካ እወዳለሁ። ስለዚህ ስለ ክርስቶስ በድካም በመንገላታትም በችግርም በስደትም በጭንቀትም ደስ ይለኛል ፤ ስደክም ያን ጊዜ ኃይለኛ ነኝና። ፪ቆሮ.፲፪፡፩-፲

Copyright © 2009 Debre Selam Medhanealem Ethiopian Orthodox Tewahedo Church 4401 Minnehaha Avenue South Minneapolis, Minnesota 55406 Tel. (612) 721-1222 (U.S.A)

- ቅዱስ ጳውሎስ ለመንፈስ ልጁ ለጢሞቴዎስ ሰማዕት ሆኖ እንደሚያልፍ እንደነገረው፡- በመሥዋዕት እንደሚደረግ ፥ <u>የእኔ ሕይወት ይሠዋልና ፥ የምሄድበትም ጊዜ ደርሶአል። መልካሙን ገድል ተጋድዬአለሁ ፥ ሩጫውን ጨርሼአለሁ ፥ ሃይማኖትን ጠብቄአለሁ ፤ ወደ ፊት የጽድቅ አክሊል ተዘጋጅቶልኛል ፥</u> ይህንም ጻድቅ ፈራጅ የሆነው ጌታ ያን ቀን ለእኔ ያስረክባል ፥ ደግሞም መገለጡን ለሚወዱት ሁሉ እንጂ ለእኔ ብቻ አይደለም። ፪.ጢሞ.፬፡፮-፰
- የሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ደቀ መዛሙርት፡-

  - ጢሞቴዎስ
    - ፊልጵ.፪፡፲፱-፳ ፤
    - ፪ቆሮ.፩፡፩ ፤
    - ሐዋ.፲፱፡፳፪ ፤
    - ዕብ.፲፫፡፳፫ ፤
    - ፩ጢሞ.፭፡፳፫ ፤
    - ፩ጢሞ.፬፡፲፪
  - ቲቶ
    - ቲቶ፩፡፬
    - ፩ጢሞ.፩፡፲፰
  - ቲኪቆስ
    - ኤፌ.፮፡፳፩
    - ቆላ.፬፡፯
    - ቲቶ.፫፡፲፪
    - ፪ጢሞ.፬፡፲፪

ከላይ ከተዘረዘሩት ሌላ በተለያዩ መልእክታት ውስጥ የተጠቀሱ የሐዋርያው ደቀ መዛሙርት አሉ። አብዛኛውን ለመጥቀስ ያህል ሐዋርያው ወደ ሮሜ ሰዎች ከላከላቸው መልእክት ምዕራፍ አሥራ ስድስትን ከቁጥር አንድ እስከ ሃያ ሦስት መመልከት ያስፈልጋል። ሮሜ ፲፮፡፩-፳፫

**ወስብሐት ለእግዚአብሔር!!**

**የደብረ ሰላም መድኃኔዓለም ሰንበት ትምህርት ቤት ትምህርት ክፍል**

ይህ ጽሑፍ ለብዙ ዓመታት በእንዲህ ዓይነት ሁኔታ እንዲጻፍ ትምህርት ክፍሉ ብዙ ጊዜ አስቧል። እግዚአብሔር በፈቀደው ቀንና ሰዓት ሁሉ ነገር አሁን ተፈጽሟል።

ምንጭ፡-

- መጽሐፍ ቅዱስ
- ጥሩ ምንጭ (ኅሩይ ወልደ ሥላሴ) ፲፱፻፺፯
- SAINT PETER AND PAUL (POPE SHENOUDA)

Copyright © 2009 Debre Selam Medhanealem Ethiopian Orthodox Tewahedo Church 4401 Minnehaha Avenue South Minneapolis, Minnesota 55406 Tel. (612) 721-1222 (U.S.A)